# ቴዎድሮስ አድሃኖም "አንዳርጋቸው ጽጌን በመኪና እያዞርን ልማቱን እያስጎበኘነው ነው" አሉ

**"ለአንዳርጋቸው ፅጌ ላፕቶፕ ገብቶለት መፅሀፍ ፅፎ ኦልሞስት ጨርሷል"**

**"በመኪና እየዞረ የሀገሪቱን ልማት ያያል። አዳማ ላይ ልማቱን አይቶ ተደንቋል።"**



የአሜሪካ ድምጽ ራድትዮ እንደዘገበው በኢትዮጵያ እስር ቤት የሚገኙት የግንቦት ሰባት ዋና ጸሐፊ አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ በተሻለ ሁኔታ መያዛቸዉን የአገሪቱ ዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ቴዎድሮስ

አድሃኖም ገለጹ።

ሚኒስትሩ ትላንት ለአሜሪካ ድምጽ ራዲዩ የአማርኛዉ ቋንቋ ስርጭት ስለ ፕሬዚደንት ኦባማ ኢትዮጵያ ጉብኚት በሰጡት ቃለ ምልልስ ስለ አቶ አንዳርጋቸዉ አያያዝ ተጠይቀዉ ፣ ታሳሪዉ በመኪና ሆነዉ አገሪቱ በልማት እያደረገች ያለችዉን ግስጋሴ እንዲጎበኙ ሁሉ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

አቶ አንዳርጋቸዉ ፍርድ ፊት ለመቅረብ ፣ የህግ ጥብቅና ለማግነትና በቤተሰብ ለመጎብኘትስ ችለዋል ወይ ሲል ላቀረበላቸው ጥያቄ ዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቴዎድሮስ የሚከተለዉን መልሰዋል።

የእንጊግሊዝ ዜግነት ያላቸዉ የግንቦት ሰባት ዋና ጸሐፊ አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ ከአንድ ዓመት በፊት ሰኔ 2006 ዓም የመን ዉስጥ በኢትዮጵያ ጸጥታ ሃይሎች ተይዘዉ መወሰዳቸዉ ይታወሳል። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ሁለት ጊዜ ብቻ በኢትዮጵያ የእንግሊዝ ኤምባሳ ባለስልጣናት እንደተጎበኙ ተገልጿል። የብሪታኒያ መንግስት በቅርቡ ባወጣዉ መግለጫ የዜጋዉ የአንዳርጋቸዉ ጽጌ ጉዳይ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ባለዉ ግንኙነት አሉታዊ እንደምታ እንዳያስከትል መናገሩ አይዘነጋም።

የአሜሪካ ድምጽ ራድዮ ዘገባን ያድምጡ:-

- See more at: http://www.zehabesha.com/amharic/archives/45438#sthash.OpINPOx9.dpuf